# COMMUNITY PARTNERS PROGRAM

# ማህበረሰባዊ የባለድርሻዎች መርሃ ግብር

MIGRANT
RESOURCE
CENTRE
(Southern Tasmania) Inc.

## Aged Care Information Kit for the Amharic speaking Community of (Southern) Tasmania

## በደቡብዊ ታስማኒያ ለሚኖሩ አማርኛ ተናጋሪ የማህበረሰብ ኣባላት የኣረጋውያንን እንክብካቤ በሚመለከት የተዘጋጀ የመረጃ ስብስብ

# Migrant Resource Centre

## (Southern Tasmania) Inc.


**Address: 49 Molle Street**

**Hobart, TAS 7000**

**Phone: 03-6221 0999**
**Fax: 03-6231 1264**


***This resource kit was produced by:***


*Migrant Resource Centre*

*Community Partners Program (CPP)*

*with translations into Amharic by CPP and Multimedia Languages & Marketing*

*This CPP project was funded by the*
*Australian Government Department of Health and Ageing*
*under the Community Partners Program.*

## Index ቅጥያ


1. Community Partners Programme - CPP
   ማህበረሰባዊ የባለድርሻዎች መርሃ ግብር

2. Aged Care Services in Australia
   በኣውስትራሊያ የኣረጋውያን እንክብካቤ ኣገልግሎት

3. Home and Community Care - HACC
   የቤትና የህብረተሰብ እንክብካቤ

4. Community Aged Care Packages - CACP
   የህብረተሰብ የኣረጋውያን እንክብካቤ ማእቀፍ

5. Extended Aged Care at Home packages – EACH
   ቤት ለቤት የሚሰጥ ሰፋ ያለ የኣረጋውያን እንክብካቤ ማእቀፍ

6. Extended Aged Care at Home for Dementia packages – EACHD
   በእድሜ ምክንያት ኣዕምሮኣቸውን ለሚስቱ ቤት ለቤት የሚሰጥ ሰፋ ያለ የኣረጋውያን እንክብካቤ ማእቀፍ

7. Respite Care
   ጊዚያዊ የማቆያ ቤት እንክብካቤ

8. CBS Homeshare
   ሲቢኤስ የማዳበል ኣገልግሎት

9. Aged Care Assessment Teams
   የኣረጋውያን እንክብካቤ ምዘና ቡድኖች

10. Residential Aged Care
    አረጋውያን እንክብካቤ እያገኙ የሚኖሩበት ማእከል

11. Retirement Villages / Independent Living Units
    የመጦሪያ መንደሮች/የግል መኖሪያ ቤቶች

12. MRC Home and Community Care - HACC
    በስደተኞች የመረጃ ማእከል የቤትና የማህበረሰብ እንክብካቤ

13. MRC Community Aged Care Packages - CACP
    በስደተኞች የመረጃ ማእከል ማህበረሰባዊ የኣረጋውያን እንክብካቤ ማእቀፎች

Other useful information
ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎች

14. Useful telephone numbers
ጠቃሚ የስልክ ቁጥሮች
15. Commonwealth Carelink Centre
የጋራ ብልፅግና ሴንተርሊንክ ማእከል

16. 5 Steps to Aged Care
ለኣረጋውያን እንክብካቤ ኣምስት ደረጃዎች

17. Costs of residential aged care
የኣረጋውያን እንክብካቤ መስጫ ተቋማት ዋጋ

18. Aged Care Advocacy
የኣረጋውያን እንክብካቤ ጥብቅና

19. Aged Care complaints resolution scheme
የኣረጋውያን እንክብካቤ የቅሬታ ዎች መፍትሄ ኣሰጣጥ

20. What is Dementia?
ዳይመንሺያ ምንድነው?
Diagnosing Dementia
ዳይመንሺያን መርምሮ ማወቅ
Early planning
የቅድሚያ እቅድ
Changing behaviours
ባህርይን መቀየር
Communication
ግንኙነት
Taking a break
እረፍት መውሰድ
Communication Poster

# 1. Community Partners Program

**What is Community Partners Program (CPP)?**

- CPP can support older people from your community to access aged care services.

- CPP can help older people from your community, who are thinking about moving into residential aged care facilities.

- CPP can help people from your community to feel at home when they move into residential aged care facilities.

- CPP can also help your community find out more about aged care services.

**How can I contact CPP?**

- Please call Community Partners Program Project Officer at the Migrant Resource Centre:
- Address: 49 Molle Street
  Hobart 7000
  Phone: (03) 6221 0999

# ማህበረሰባዊ የባለድርሻዎች መርሃ ግብር

**ማህበረሰባዊ የባለድርሻዎች መርሃ ግብር**

**(Community Partners Program (CPP) ምንድነው?**

- CPP በማህበረሰብዎ ውስጥ ያሉት ኣዛውንቶች የኣረጋውያን እንክብካቤ ኣግልግሎት እንዲያገኙ ያግዛል።
- CPP ወደ ኣረጋውያን መኖሪያ መዛወር የሚፈልጉ በማህበረሰብዎ ውስጥ ያሉትን ኣዛውንቶች ይረዳል።
- CPP በማህበረሰብዎ ውስጥ ያሉት ኣረጋውያን እንክብካቤ ወደ ሚያገኙበት የመኖሪያ ኣገልግሎት ሲሄዱ "በክሮኦሺያኖች ቅድ"' በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ እንዳሉ እንዲሰማቸው እገዛ ይሰጣል።
- CPP ስለ ኣረጋውያን የእንክብካቤ ኣገልግሎቶች የሚያስፈልገውን መረጃ በመስጠት ማህበረሰብዎን ይረዳል።

**የCPPን ኣድራሻ እንዴት ማግኘት እችላለሁ?**

- እባክዎትን በስደተኞች የመረጃ ማእከል ውስጥ የሚገኘውን ማህበረሰባዊ የባለድርሻዎች መርሃ ግብር ፕሮጀክት ሰራተኛ ደውለው ያነጋግሩ
- ኣድራሻው

49 Molle Street

Hobart 7000

የስልክ ቁጥር :(03) 6221 0999

# 2. Aged Care services in Australia

Most older Australians prefer to remain living in their own home, with the support of family, friends and aged care services. Living in a modern Australian society however, most adult family members work and are consequently often unable to be fully responsible for the care of their elderly relatives. The Australian federal and state governments therefore provide funding to ensure that quality aged care services are available.

Many aged care services are designed to enable older people to stay at home and live independent lives. When high care needs mean that it is no longer possible for an elderly person to remain at home, high quality residential aged care facilities are available.

# የአረጋውያን የእንክብካቤ ኣገልግሎቶች በኣውስትራሊያ

ኣብዛኞቹ ኣውስትራሊያውያን በቤተሰቦቻቸው፣ በጓደኞቻቸውና የኣረጋውያን እንክብካቤ ሰጭ ተቋሞች ኣገልግሎት እያገኙ በግል መኖሪያ ቤታቸው ውስጥ መኖርን ይመርጣሉ። በዘመናዊው የኣውስትራሊያ ኑሮ ግን ኣብዛኞቹ ለኣካለ መጠን የደረሱ የቤተሰብ ኣባላት የሚሰሩ ስለሆነ ክዚህ በተጨማሪ ኣረጋውያን ዘመዶቻቸውን ሙሉ በሙሉ ሃላፊነት ወስደው ለመንከባከብ ይቸገራሉ። የኣውስትራሊያ ፌደራላዊ መንግስትና የክልሉ ማንግስታት ይሄንን ችግር ለመፍታት ጥራታቸውን የጠበቁ የኣረጋውያን ተንከባካቢ ተቋማት እንዲኖሩ ገንዘብ ይመድባል።

ኣብዛኞቹ የኣረጋውያን ተንከባካቢ ተቋማት የተቋቋሙት ኣረጋውያን ኣስፈላጊውን እንክብካቤ እያገኙ በግል መኖሪያ ቤታቸው ውስጥ እንዲኖሩ በሚያስችል መንገድ ነው። ከፍ ያለ እንክብካቤ የሚፈልጉ ኣረጋውያን ኣሉ ማለት ደግሞ ይህን ኣግልግሎት በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ በመሆን በቀላሉ ማግኘት ስለማይቻል ኣረጋውያኑ በመኖሪያ ቤታቸው መቆየት ኣይችሉም። ስለዚህ ከፍተኛ ጥራት ያላቸው የኣረጋውያን እንክብካቤ መስጫ ኣገልግሎቶች ተቋቁመዋል።



# 3. Home and Community Care – (HACC)

The HACC program provides community care services to elderly people, disabled people and carers. HACC can provide a range of services that can include help with housework, personal care, meals, transport and social support at home or through Day Centres.

## የቤትና የማህበረሰብ እንክብካቤ

የHACC መርሃ ግብር የማህበረሰባዊ እንክብካቤ ኣግልግሎት ለኣረጋውያን፣ የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎችና ለተንካባካቢዎቻቸው ይሰጣል። HACC ዘርፈ ብዙ የሆነ ኣገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን የቤት ስራን፣ የግል እንክብካቤን፣የምግብ ዝግጅትን፣ የመጓጓዣንና ሌሎች ማህበራዊ ድጋፎችን ያካተተ ኣግልግሎት በቤት ወይም በመዋያ ማእከላት ይሰጣል።



# 4. Community Aged Care Packages – (CACP)

A CACP is an individually tailored package of care services which helps people with complex care needs to stay living at home. The care is provided in home, but is of a similar level of intensity as low level residential aged care.

# ማህበረሰባዊ የኣረጋውያን እንክብካቤ ማእቀፎች

ማህበረሰባዊ የኣረጋውያን እንክብካቤ ማእቀፎች CACP በግለሰብ ደረጃ የሚሰጥ የእንክብካቤ ኣገልግሎት ሲሆን የሚያተኩረውም በቤታቸው ውስጥ ሆነው ከፍተኛ እርዳታ ማግኘት ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ነው። ኣገልግሎቱ የሚሰጠው በቤት ውስጥ ቢሆንም ደረጃው ዝቅ ያለ የኣረጋውያን መኖሪያ ማእከል ውስጥ የሚሰጠውን የኣገልግሎት ደረጃ ያህል ይሰጣል።



# 5. Extended Aged Care at Home Packages - (EACH)

The EACH program has a limited capacity. EACH packages provide a high level of care that enables frail aged people to remain living at home.

## እቤት ውስጥ የሚሰጡ ሰፋ ያሉ የአረጋውያን እንክብካቤ ማእቀፎች

EACH መጠነኛ አቅም ያለው መርሃ ግብር ነው። የEACH ማእቀፎች በጣም ከፍተኛ ደረጃ ያለው እንክብካቤ የሚሰጡ ሲሆን፤ በጣም የደከሙ አረጋውያን በቤታቸው ውስጥ ሆነው እንዲረዱ የሚያስችል ነው።



# 6. Extended Aged Care at Home for Dementia Packages - (EACHD)

***Extended Aged Care at Home Packages for Dementia (EACHD)*** - *The EACHD program has a limited capacity. EACHD packages provide a high level of care that enables frail aged people with Dementia to remain living at home.*

# በእድሜ ምክንያት ኣዕምሮኣቸውን ለሚስቱ እቤት ውስጥ የሚሰጡ ሰፋ ያሉ የኣረጋውያን እንክብካቤ ማእቀፎች

**በእድሜ ምክንያት ኣዕምሮኣቸውን ለሚስቱ እቤት ውስጥ የሚሰጡ ሰፋ ያሉ የኣረጋውያን እንክብካቤ ማእቀፎች** (EACHD)።

EACHD **መጠነኛ ኣቅም ያለው መርሃ ግብር ነው። የ**EACHD **ማእቀፎች በጣም ከፍተኛ ደረጃ ያለው እንክብካቤ የሚሰጡ ሲሆን ፣ በጣም የደከሙና በእድሜ ምክንያት ኣዕምሮኣቸውን የሳቱ ኣረጋውያን በቤታቸው ውስጥ ሆነው እንዲረዱ የሚያስችል ነው።**



# 7. Respite Care

## ጊዚያዊ የማቆያ ቤት እንክብካቤ

Respite is an option for elderly people who live at home but require short-term residential care, possibly due to a carer's illness or absence.

## ጊዚያዊ የማቆያ ቤት እንክብካቤ

ጊዚያዊ የማቆያ ቤት እንክብካቤ በቤታቸው ውስጥ የሚኖሩ አረጋውያን ለአጭር ጊዜ እንክብካቤ ሊያገኙ የሚችሉበት አማራጭ ማእከል ነው። ይህ አግልግሎት የሚሰጥበት ዋና ምክንያት ብዙ ጊዜ የቤት ውስጥ ተንከባካቢው ሰው ሲታመም ወይም መምጣት ሳይችል ሲቀር ነው።



# 8. CBS Homeshare

CBS Homeshare knows that older people would prefer to stay at home as long as possible. Sometimes they might like to have company and a bit of help. Young People who come from Overseas to work or to study in Australia are often looking for accommodation. If you have a spare room and would like to have a young person come to live with you, CBS Homeshare can assist you. In return for free accommodation, the young person undertakes to help you for 10 hours a week doing housework, gardening or going shopping. Ongoing costs such as electricity and food are shared.

You can be sure that the young person's character, personality and habits have all been taken into consideration to determine whether the young person is suitable to live with an older person. You will have a contract setting out all the house rules and if you have any queries or problems, you can contact the co-ordinator at any time.

A fee of $150 is payable for arranging Homeshare, but this can be paid by instalments.

For more information contact:
Vivien Beattie
Homeshare Coordinator,
Community Based Support Services,
Tel: 03 6208 6600
Email Homeshare@cbssouth.com.au.

# ሲቢኤስ  የማዳበል  ኣገልግሎት

CBS የማዳበል ኣገልግሎት ኣረጋውያን  በተቻለ መጠን እቤታቸው ውስጥ  መኖርን እንደሚመርጡ ያውቃል። ኣንዳንድ ጊዜ ከሰው ጋር ኣብሮ መቆየትና ኣንስተኛ እርዳታ ማግኘት ይፈልጋሉ። ለስራ ወይም ለትምህርት ከውጭ ኣገር የሚመጡ ወጣቶች ደግሞ የመኖሪያ ቤት ይፈልጋሉ። ትርፍ የመኖሪያ ክፍል ካልዎትና ኣንድ ወጣት ኣብረዎት እንዲኖር የሚፈልጉ ከሆነ CBS የማዳበል ኣገልግሎት ሊረዳዎት ይችላል። በነፃ ለሚሰጡት መኖሪያ ክፍል ዋጋ ወጣቱ በሳምንት የ10 ሰዓታት  የቤት ውስጥ፣ የጓሮ ኣትክልት ወይም  ገበያ በመሄድ  የስራ ኣግልግሎት ይሰጣል። እንደ መብራት፣ ምግብና የመሳሰሉት ወጭዎች በጋራ ይሸፈናሉ።

የወጣቱ ባህርይ፣ ስብእናና ጠባይ ከሽማግሌ ጋር ተስማምቶ እንዴት መኖር እንደሚችል ለመወሰን ግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ነገሮች መኖራቸውን እርግጠኛ መሆን ያስፈልጋል። ከቤቱ ደምብ በተጨማሪ የኮንትራት ውል ይኖራል። ሌላ ጥያቄ ወይም ችግር ካለ ደግሞ ኣስተባባሪውን በማንኛውም ሰዓት ደውሎ ማግኘት ይቻላል።

የማዳበሉን ስራ ለመስራት የ150 ዶላር ክፍያ ኣለው ፤ ክፍያውም ቀስ በቀስ ሊከፈል ይችላል።

ለተጨማሪ መረጃ

Vivien Beattie
Homeshare Coordinator,
Community Based Support Services,
**በስልክ ቁጥር**: 03 6208 6600
**በኢ-ሜይል** Homeshare@cbssouth.com.au. ማግኘት  ይችላሉ

# 9. Aged Care Assessment Team - (ACAT)

To access Community Aged Care Packages (CACPs), Extended Aged Care at Home (EACH) packages, or to move into a residential aged care facility you need to be assessed by an Aged Care Assessment Team (ACAT).

**WHAT IS ACAT?**

Aged Care Assessment Teams (ACATs) are teams of health professionals who provide information and advice to older people who are having difficulty living at home.

ACATs may consist of geriatricians, general practitioners, psychologists, nurses, social workers, physiotherapists and occupational therapists. They will usually make an appointment to see you in your home or, if you are in hospital, they will visit you there.

ACATs assess your specific care and health needs.

They will provide information on suitable care options and arrange appropriate referrals to local community services.

They advise you on what type of Australian Government funded services you need to help you continue living in your home or whether you should enter an aged care home. The final decision, however, remains with you.

Visits and assessments by ACATs are FREE.

**HOW DO I CONTACT ACAT?**

Information about the ACAT is available from the Commonwealth Carelink Centres on 1800 052 222 or you can ring Aged and Community Care Information Line on 1800 500 853.

| |
|---|
| ACATs IN TASMANIA: |
| Hobart – 03 6222 7274 |
| Northern Tasmania – 03 6336 4144 |
| North West Tasmania – 03 6429 8400 |

If you need assistance regarding ACAT, please contact the Community Partners Program at the Migrant Resource Centre.

(Reference: www.seniors.gov.au and the booklet of "Quality Care For Older Australians" printed by the Department of Health and Aged Care)

# የአረጋውያን እንክብካቤ ምዘና ቡድን

ማህበረሰባዊ የአረጋውያን እንክብካቤ ማእቀፎች(CACPs), እቤት ውስጥ የሚሰጥ ሰፋ ያለ የአረጋውያን እንክብካቤ ማእቀፍ(EACH) ወይም ወደ መደበኛው የአረጋውያን እንክብካቤ መስጫ ተቋም ለመግባት በአረጋውያን እንክብካቤ ምዘና ቡድን(ACAT) ሊገመገሙ ይገባል።

**የአረጋውያን እንክብካቤ ምዘና ቡድን(ACAT) ምንድነው?**

የአረጋውያን እንክብካቤ ምዘና ቡድኖች(ACATs) ማለት በቤታቸው ውስጥ ለመኖር ችግር ያለባቸው አረጋውያንን አስፈላጊውን መረጃና ምክር የሚሰጡ የጤና ባለሞያዎች ያሰባሰቡ ቡድኖች ናቸው።

ACATs የአረጋውያን የጤና ስፔሺያሊስቶች (geriatricians) ፣ የአጠቃላይ ህክምና ባለሞያዎች (general practitioners) ፣ሳይኮሎጂስቶች፣ ነርሶች፣ የማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኞች (social workers )፣ የአካል እንቅስቃሴ ብቃት ሃኪሞች physiotherapists)፣ የስራ ብቃት ሃኪሞች (occupational therapists) ያካትታል። ብዙ ጊዜ እቤትዎ ድረስ መጥተው ለማየት ቀጠሮ ይሰጣሉ ወይም እርስዎ ሆስፒታል ውስጥ ከሆኑም መጥተው ይጎበኙዎታል።

ACATs እርስዎን የሚያስፈልግዎትን የግል እንክብካቤና የጤና አግልግሎት ይዳስሳሉ።

የአውስትራሊያ መንግስት የገንዘብ ድጎማ ከሚያደርግላቸው እርዳታዎች ውስጥ በየትኛው በቀጣይነት ቢኖሩ እንደሚሻልዎት፤ ማለትም በቤትዎ ውስጥ ወይም በአረጋውያን እንክብካቤ ማእከል ውስጥ ለመኖር እንዲመርጡ አስፈላጊውን ምክር ይሰጣሉ። የመጨረሻው ውሳኔ ግን የእርስዎ ይሆናል።

በACATs የሚደረጉ ጉብኝቶችና ምዘናዎች ከክፍያ ነፃ ናቸው።

**ACATን ኣድራሻ እንዴት ማግኘት እችላለሁ?**

ACATን **በሚመለከት** Commonwealth Carelink Centres **በስልክ ቁጥር** 1800 052 222 **ወይም ደግሞ** Aged and Community Care Information Line **በስልክ ቁጥር** 1800 500 853. **በመደወል ኣስፈላጊውን መረጃ ማግኘት ይችላሉ።**

| |
|---|
| ACATs IN TASMANIA:<br><br>Hobart - 03 6222 7274<br><br>Northern Tasmania - 03 6336 4144<br><br>North West Tasmania - 03 6429 8400 |

ACATን **በሚመለከት እርዳታ ከፈለጉ እባክዎትን በስደተኞች የመረጃ ማእከል ማህበረሰባዊ የባለድርሻዎች መርሃ ግብር ይደውሉ።**

**(ለተጨማሪ መረጃ** www.seniors.gov.au **እና 'ለኣውስትራሊያ ኣረጋዊያን ጥራት ያለው ኣገልግሎት መስጠትን" በሚመለት በጤናና በኣረጋውያን ሚኒስቴር የታተሙ በራሪ ወረቀቶች ይመልከቱ።)**

# 10. Residential Aged Care

Residential Aged Care facilities are available to those who can no longer remain in their own home. Facilities can provide either low or high level care. High level care in a residential facility provides 24 hour a day nursing care and includes the provision of meals, personal care, laundry, activities and entertainment. The level of care in residential aged care facilities is of a very high standard in Australia. Facilities are required to meet the physical, emotional, spiritual and cultural needs of their residents.

# አረጋውያን እንክብካቤ እያገኙ የሚኖሩበት ማእከል

በግል መኖሪያ ቤታቸው ውስጥ መኖር ለማይችሉ አረጋውያን እንክብካቤ እያገኙ የሚኖሩባቸው ማእከላት ተዘጋጅተውላቸዋል።ማእከላቱ ዝቅተኛም ከፍተኛም ደረጃ እንክብካቤ የሚሰጡባቸው ሊሆኑ ይችላሉ። ከፍተኛ ደረጃ እንክብካቤ የሚሰጡባቸው ማእከላት በየቀኑ ለ24 ሰዓታት እንክብካቤ የሚሰጥባቸው ሲሆን፤ የምግብ፣ የግል እንክብካቤ፣የልብስ ኣጠባና የማዝናናት ኣገልግሎቶችን ይሰጣሉ። በኣውስትራሊያ የኣረጋውያን የመኖሪያ ማእከላት  የሚሰጠው እንክብካቤ በከፍተኛ ደረጃ ደረጃውን የጠበቀ ነው። በተቋሞቹ ውስጥ የሚገኙ የኣገልግሎት መስጫ መሳለጫዎች የነዋሪዎቹን የኣካል፣ የኣእምሮ፣ መንፈሳዊና ባህላዊ ፍላጎቶቻቸውን በሚያሟላ መልኩ የተዘጋጁ ናቸው።



# 11. Retirement Village / Independent Living Units

Retirement Village / Independent Living Units - similar to private apartments but may offer some services such as laundry, cleaning and personal care.

All aged care services in Australia are required to meet strict standards and follow guidelines that ensure elderly people are receiving the best possible care and that their well-being and quality of life is protected.

# የመጦሪያ መንደር/ራሳቸውን የቻሉ የግል መኖሪያ ቤቶች

የመጦሪያ መንደር/ራሳቸውን የቻሉ የግል መኖሪያ ቤቶች፤ ከግል የመኖሪያ ቤቶች ተመሳሳይ ሲሆኑ ነገር ግን እንደ ልብስ ኣጠባ፣ ፅዳትና የግል እንክብካቤ የመሳሰሉትን ኣገልግሎቶች ይሰጣል።

በኣውስትራሊያ የሚገኙት ሁሉም የኣረጋውያን እንክብካቤ መስጫ ተቋማት መሰረታዊ የኣገልግሎት ደረጃቸውን በሚገባ ማሟላትና፤ በተቻለ መጠን ኣረጋውያኑ ሊያገኙ የሚገባቸውን ከፍተኛ እንክብካቤ፣ ደሕንነታቸውንና የኑሮ ደረጃቸውን እንዲሟላ በሚጠይቀው መመሪያና መስፈርት መሰረት መጠበቁን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል።



# 12. Migrant Resource Centre Home and Community Care (HACC)

Provides services for people from non-English speaking backgrounds who are

- frail aged
- younger disabled
- carers

### What is Community Partners Program (CPP)?

CPP can support older people from your community to access aged care services.

CPP can help older people from your community, who are thinking about moving into residential aged care facilities.

CPP can help people from your community to feel at home in the German style when they move into residential aged care facilities.

CPP can also help your community find out more about aged care services.

### What Can HACC Provide For You?

HACC provides a range of services that can include help with house-work, personal care, meals, transport and social support at home or through Day Centres.

### What Does MRC / HACC Do?

It provides information and practical help to people from diverse cultural and linguistic backgrounds who are frail aged, younger disabled, and their carers to remain in their own home.

### We Can Help You:

## Client Worker

- With inquiries and to fill in forms
- Find out about available services
- Assess your eligibility and refer you to services, and co-ordinate services
- Obtain advice, information, and assistance with advocacy issues
- Provide a befriending service offered by our volunteers
- Healthy Living Program activities
- Pontville Cemetery visits
- Transport may be provided at a reasonable cost.

## Community Development Officer

How can the Community Development Officer work with your community?

- Learn about and use HACC and other aged care services.
- Plan and develop programs that meet your needs and improve quality of life.
- Help government and service providers to understand your community's needs.

## Multicultural Seniors' Club / Day Centre

- The Multicultural Day Centre is a social club for MRC / HACC clients.
- Members meet weekly on Tuesday at the Croatian Club, Wednesday at the German Club, Thursday at the Chinese Club or the Multicultural Club on Friday from 10.00 am to 2.00 pm at the Migrant Resource Centre.
- A hot lunch is provided at a reasonable cost, as well as activities ranging from entertainment and exercise to health and information, including outings for lunch.
- Transport may be provided at a reasonable cost, normally $ 4.00 per trip.
- There is a limit to the number of clients we can cater for.

- We would like people who are interested in joining to first contact the Day Centre Co-ordinator on phone 6234 9411.

| | | |
|---|---|---|
| **Day Centre Lunch –** | **$10.00** | |
| **HACC Fees –** | **$2.00** | **(subject to waiver)** |
| **Transport -** | **$6.00** | **(return most trips)** |

## Bi-cultural Workers

- Provide a link between our clients and our services.
- Bi-cultural workers help us to provide our service in a way that suits your culture and language.
- Chinese / Vietnamese, Serbian and German Bi-cultural workers assist at the Multicultural Seniors' Day Centre and assist the Case-worker.

## How Can You Get Help From MRC HACC?

You can contact us yourself or, a person can contact us on your behalf, such as

- your doctor
- a relative
- a friend
- the community health nurse

MRC HACC can also provide help to migrant communities.

## Interpreters

We work closely with the Translating and Interpreting Service (TIS) which can provide interpreters on site or by telephone.

## Confidentiality

All personal information entrusted to us is kept confidential.

### How Can You Contact Our Service?

**You can contact us by**

- Phone (03) 6221 0999
- Fax (03) 6231 1264
- Letter
- Email reception@mrchobart.org.au
- Come in to our office between
- 9.00 am – 5.00 pm

Migrant Resource Centre
(Southern Tas) Inc
49 Molle Street
Hobart Tas 7000

# በስደተኞች የመረጃ ማእከል የቤትና የማህበረሰብ እንክብካቤ

HACC እንግሊዝኛ ተናጋሪ ካልሆነ ህብረተሰብ ለመጡና

- በጣም ለሸመገሉ
- የአካል ጉዳት ላለባቸው ወጣቶችና
- ለተንከንካባካቢዎች የተለያየ አገልግሎት ይሰጣል።

### ማህበረሰባዊ የባለድርሻዎች መርሃ ግብር (CPP) ምንድነው?

CPP በማህበረሰብዎ ውስጥ የሚገኙ አዛውንቶች የአረጋውያን እንክብካቤ ተቋማት ማግኘት እንዲችሉ ይረዳል።

CPP በማህበረሰብዎ ውስጥ የሚገኙ አዛውንቶች ወደ አረጋውያን እንክብካቤ መስጫ ተቋማት መግባት የሚፈልጉትን ይረዳል።

CPP በማህበረሰብዎ ውስጥ የሚገኙ አዛውንቶች ወደ አረጋውያን እንክብካቤ መስጫ ተቋማት ውስጥ ሲገቡ " በጀርመን ቅድ" በቤታቸው ውስጥ እንዳሉ እንዲሰማቸው ይረዳል።

CPP ማህበረሰብዎ ስለ አረጋውያን እንክብካቤ መስጫ ተቋማት የበለጠ እንዲያውቁ ይረዳል።

### HACC ምን ሊያደርግልዎት ይችላል?

HACC እንደ ቤት ስራ፣ የግል እንክብካቤ፣ የምግብ፣ የመጓጓዣ፣ የማህበራዊና የመሳሰሉት የተለያዩ ዓይነት አገልግሎቶች በየቤቱ ወይም በቀን መዋያ ስፍራዎች ይሰጣል።

### MRC / HACC ምን ይሰራል?

ከተለያየ ባህልና ቋንቋ ስብጥር ለመጡ በጣም ለሸመገሉ፣የአካል ጉዳት ላለባቸው ወጣቶችና  እንዲሁም ለተንከንካባካቢዎቻቸው በየቤቶቻቸው እያሉ በቂ መረጃና ተጨባጭ የሆነ እርዳታ ይሰጣል።

### የሚከተሉትን እገዛዎችን እንሰጣለን፤

## በደንበኞች  ሰራተኛ የሚከናወኑ ተግባራት፡

- ፎርም በመሙላትም ሆነ ስለሚያጋጥሙ የተለያዩ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት።
- ለነዋሪነት የሚያስፈልጉ ምዘናዎችን የማድረግና ሌሎች ኣግልግሎቶች እንዲያገኙ የማስተላለፍና ኣገልግሎቶችን ማቀናጀት።
- ምክር፣ መረጃ መስጠትና የጥብቅና ጉዳዮችን በሚመለከት ድጋፍ መስጠት
- የበጎ ፈቃደኞች መልካም ኣግልግሎት በሚገባ መስጠት
- ለጤናማ ኑሮ የሚረዱ የስራ መርሃ ግብሮችን ማዘጋጀት
- ፖንትቪል የመቃብር ቦታ ማስጎብኘት
- በተመጣጣኝ ዋጋ የትራንስፖርት ኣገልግሎት መስጠት

## በማህበረሰብ ልማት ባለሞያ የሚከናወኑ ተግባራት፡

የማህበረሰብ ልማት ባለሞያ ከማህበረሰባችሁ ጋር እንዴት ይሰራል?

- HACC ምን እንደሆነ በሚገባ በማወቅ HACCንና ሌሎች የኣረጋውያን እንክብካቤ ተቋሞችን በመጠቀም
- የእርስዎን ፍላጎት የሚያሟላና የኑሮዎ ሁኔታ የሚሻሽል መርሃ ግብር በማቀድ ያዘጋጃል
- መንግስትንና ሌሎች ኣገልግሎት መስጫ ተቋሞች የማህበረሰብዎን ፍላጎት ምን እንደሆነ እንዲረዱ ይረዳል።

## የኣዛውንቶች ህብረ- ባህላዊ ክበቦች ወይም የቀን መዋያዎች

- ህብረ- ባህላዊ የቀን መዋያ ማእከል ለ MRC / HACC  ደምበኞች  ማህበራዊ ክበብ ነው።
- ኣባላት በየሳምንቱ  ዘወትር ማክሰኞ በክሮሺያ ክበብ ፣ዘወትር ረቡዕ በጀርመን ክበብ፣ ዘወትር ሓሙስ በቻይና ክበብ ወይም በህብረ- ባህላዊ ክበብ ዘወትር ኣርብ ከጧቱ 10፡00 እስከ ከሰዓት 2፡00 በስደተኞች የመረጃ ማእከል።
- ትኩስ ምሳ በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲሁም መዝናናትን፣ ለጤና የሚረዱ የሰውነት እንቅስቃሴዎችና መረጃዎችን የሚያገኙበትንና ምሳ ያካተተ ሽርሽር ይኖራል።
- ተመጣጣኝ  በሆነ ዋጋ መጓጓዣ ይቀርባል ብዙ ጊዜ ለያንዳንዱ ጉዞ በ $4.00  ነው።
- ማስተናገድ የምንችለው የደንበኞች ቁጥር የተወሰነ ነው።
- በዚህ ጉዞ መሳተፍ የሚፈልጉ ሰዎች በስልክ ቁጥር 6234 9411   የቀን መዋያ ማእከሉ ሃላፊን በመደወል ሊያነጋግሩ ይችላሉ።

የቀን መዋያ ማእከል ምሳ $ 10.00
HACC ክፍያ — $2.00 (ሊቀያየር ይችላል)
መጓጓዣ ክፍያ - $6.00 (ኣብዛኛው ጊዜ የደርሶመልስ ነው)

## የጥንድ ባህል ሰራተኞች

- ደንበኞቻችንና ኣገልግሎታችን ያገናኛሉ
- የጥንድ ባህል ሰራተኞች ባህልዎንና ቋንቋዎን ባገናዘበ መልኩ ኣገልግሎታችን መስጠት እንድንችል ይረዱናል።

- ቻይናውያን/ቬትናማውያን፣ሰርባውያንና ጀርመናውያን የጥንድ ባህል ሰራተኞች ህብረ ባህላዊ የኣዛውንቶች ክበብ ላይ እና የያንዳንዱን ኣዛውንት ጉዳይ የሚከታተለውን ሰራተኛ ይረዳሉ

## ከMRC / HACC እርዳታ እንዴት ማግኘት ይቻላል?

ራስዎ በመደወል ሊያነጋግሩን ይችላሉ ወይም እርስዎን በመወከል ሌላ ሰው ማለትም

- ሓኪምዎ
- ዘመድዎ
- ጓደኛዎ
- የማህበረሰብዎ የጤና ነርስ ሊያነጋግረን ይችላል

MRC / HACC ለስደተኛ ማህበረሰቦች ድጋፍ ያደርጋል።

## ኣስተርጓሚ

በስልክ ወይም በኣካል የትርጉም ኣገልግሎት የሚሰጡ ኣስተርጓሚዎች (TIS) ከሚባል ተቋም እናቀርባለን።

## የምስጢር ኣጠባበቅ

እኛ ያገኘነው ማንኛቸውም የግል መረጃ ምስጢራዊነቱ የተጠበቀ ነው።

**አገልግሎታችን ማግኘት ሲፈልጉ በሚቀጥለው አድራሻ ሊያገኙን ይችላሉ**

- በስልክ ቁጥር (03) 6221 0999
- ፋክስ (03) 6231 1264
- በደብዳቤ
- በኢ-ሜይል reception@mrchobart.org.au
- ቢሮኣችን ድረስ በኣካል በመምጣት
- 9.00 am — 5.00 pm

የስደተኞት መረጃ ማእከል ድረስ በመምጣት/
Migrant Resource Centre
(Southern Tas) Inc
49 Molle Street
Hobart Tas 7000



# 13. Migrant Resource Centre Community Aged Care Packages – (CACP)

**What is the Golden Age Package Program?**
The Golden Aged Package Program is a community based program that aims to help older people to remain living in their own homes by providing flexible services to suit individual needs.

**Our Services:**
A Golden Age Package can provide several services according to what a person needs and what a person prefers. These may include:

- Personal care
- Meal preparation
- Laundry
- Housework
- Transport
- Help with shopping, visits to doctors, dentists or bill paying
- Social interaction

**Who is eligible for a Golden Age Package?**
To be eligible, your needs will first be assessed by the Aged Care Assessment Team (ACAT) to determine whether a care package is suitable for you.  This assessment is free.

**A Golden Age Package ensures that you will be:**

- Involved in deciding which services are suitable for your needs
- Able to receive services that take account of your lifestyle, culture and religious preferences;
- Invited to have a say in who provides the services in your home
- Treated with dignity and have you privacy respected;
- Free to complain about the services you receive without fear of losing services, or being disadvantaged in any way.

**How much does a Golden Age Package cost?**
Any fees charged will form part of the agreement between you and the service provider. You will not be denied a service you need because you can not afford to pay.

**For more information on the Golden Age Packages please contact:**


Migrant Resource Centre
(Southern Tas) Inc
49 Molle Street
Hobart Tasmania 7000
03 6221 0999

# በስደተኞች የመረጃ ማእከል ማህበረሰባዊ የኣረጋውያን እንክብካቤ ማእቀፎች

## የ Golden Age ማእቀፍ መርሃ ግብር ምንድነው?

የ Golden Age ማእቀፍ መርሃ ግብር ማህበረሰባዊ መሰረት ያለውና የያንዳንዱን ኣዛውንት ፍላጎት በሚስማማ መልኩ እንደ ኣስፈላጊነቱ የሚቀያየር ኣገልግሎት በመስጠት ኣረጋውያን በየቤታቸው ውስጥ እንዲኖሩ ለማገዝ እንዲቻል ዓላማ ያለው መርሃ ግብር ነው።

**ኣገልግሎታችንም፤**

የ Golden Age ማእቀፍ እያንዳንዱ ግለሰብ በሚፈልገውና በሚመርጠው መንገድ የተለያዩ ኣግልግሎቶችን ይሰጣል። ከሚሰጣቸው ኣገልግሎቶች ውሳጥ የሚከተሉት ይገኙባቸዋል፤

- የግል እንክብካቤ
- የምግብ ዝግጅት
- የልብስ ኣጠባ
- የቤት ስራ
- የማጓጓዣ ኣገልግሎት
- ገበያ ወይም ሱቅ ፣ ሃኪም ቤት፣ ወደ ጥርስ ሃኪም፣ ወደ ተለያዩ የክፍያ ቦታዎች መውሰድ
- ማህበራዊ ጉዳዮች ወደሚከናወኑበት ቦታ መውስውድ

## የ Golden Age ማእቀፍ ማንን ይመለከታል?

በዚህ መርሃ ግብር ውስጥ ለመታቀፍ በመጀመሪያ ደረጃ የእርስዎን መሰረታዊ ፍላጎት በኣረጋውያን እንክብካቤ መዛኝ ቡድን(ACAT) ተመዝኖ ማእቀፉ ለእርስዎ በትክክል የሚስማማ ስለመሆኑ ውሳኔ ይሰጥበታል። ይህም የምዘና ስራ የሚከናወነው በነፃ ነው።

## የGolden Age ማእቀፍ የሚከተሉትን ያረጋግጣል።

- ከእርስዎ ፍላጎት አንፃር ለራስዎ የሚስማማው አገልግሎት የትኛው እንደሆነ በመወሰን ላይ መሳተፍዎን
- የእርስዎን የኣኗኗር ሁኔታ፣ባህልና ሃይማኖት ባገናዘበ መልኩ አገልግሎቱን ማግኘት መቻልዎን
- በቤትዎ ውስጥ የሚፈልጉት አገልግሎት በማን መሰጠት እንደሚገባ ሃሳብ እንዲሰጡ መጋበዝዎን
- የእርስዎ የግል ክብር መጠበቁንና የግል ምስጢር መጠበቁን
- በሚያገኙት ኣግልግሎት የሚሰማዎትን ቅሬታ በማቅረብዎ፤ የሚሰጠኝ ኣገልግሎት ሊቋረጥብኝ ይችላል ብሎ ከመፍራት ወይም ሌላ መንገድ ጥቅሜ ይጓደላል ከሚል ኣስተሳሰብ ነፃ በሆነ መንገድ መግለፅዎን ያረጋግጣል።

## Golden Age ማእቀፍ ምን ያህል ውድ ነው?

ማንኛውም ክፍያ በእርስዎና በኣገልግሎት ሰጭው ድርጅት የሚደረገው ስምምነት ኣካል ነው።ገንዘብ መክፈል ባለመቻልዎ ምክንያት የሚያስፈልግዎት ኣገልግሎት ኣይነፈጉም።

## Golden Age ማእቀፍ ኣስመልክቶ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ

Migrant Resource Centre
(Southern Tas) Inc
49 Molle Street
Hobart Tasmania 7000
03 6221 0999

# Other useful Information



# ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎች

